**???? ?? ??? ?? ????? ???? ??? ? ??? ?**

**?? ? ? ???? ??? ? ?? ?? ??**

**በክልሉ የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች አደረጃጀትና**
**አሠራር ለመወሰን በድጋሚ ተሻሽሎ የወጣ**
**የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28/2008**

**ሚያዝያ/2008**
**ሀዋሳ**

## በክልሉ የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን በድጋሚ ተሻሽሎ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28/2008

### መግቢያ

የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል በሆኑ ሴቶች እና የነገይቱ ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ በሆኑ ህፃናት ውስጥ የመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነት እና የሙስና አስከፊነት ትምህርት በማስፋፋት ልማትን ለማፋጠንና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን እንዲቻል፣

የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ቢሮ በአድሱ አደረጃጀት በሴቶችና ህፃናት እና በወጣቶችና ስፖርት ቢሮዎች ተለይቶ በመደራጀቱ ቀደም ሲል የነበሩ የፀረ-ሙስና ንቅናቄ መድረኮችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣውን መመሪያ ከአሁኑ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የየቢሮውን ተቋማዊ ሥርዓት በተከተለ መልኩ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

ሙስናና ብልሹ አሠራር በክልላችን በሚካሄደው የመልካም አስተዳደር ግንባታና ቀጣይነት ላለው ልማት መረጋገጥ እንቅፋት ወደማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ እየተደረገ ባላው የፀረ ሙስና ትግል የኅብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑ ሴቶች ይበልጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል፣

ሙስናና ብልሹ አሠራር በመላው ህብረተሰብ በተለይ በሴቶች ላይ የሚያደርሰው ጉዳትና የሚያስከትለው ተጽዕኖ በርካታ በመሆኑ በፀረ ሙስና ትግሉ ግንባር ቀደም ተዋናዮች እንዲሆኑ ማስቻል ወሳኝ በመሆኑ፣

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች እና ጥምረቶች ስለሚደራጁበትና ስለሚሰሩበት ሁኔታ ለመወሰን ባወጣው ደንብ ቁጥር 84/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 4 መሠረት የክልሉን የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮችን አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን ይህ የአፈጻጸም መመሪያ በድጋሚ ተሻሽሎ ወጥቷል።

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን በድጋሚ ተሻሽሎ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 28/2008 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

**የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣**

1.‹‹**ኮሚሽን**›› ማለት የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል መንግሥት የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ነው፡፡

2.‹‹ **የመንግሥት መሥሪያ ቤት**›› ማለት በክልሉ መንግሥት በጀት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሚተዳደርና የክልሉ መንግሥት ሥራዎች የሚከናወንበት ማናቸውም መ/ቤት ነው፡፡

3.‹‹ **የመንግሥት ልማት ድርጅት** ››ማለት፡- በክልሉ መንግሥት ባለቤትነት የሚተዳደር ወይም የጥቅም ድርሻ በሙሉ ወይንም በከፊል ያለበት የልማት ድርጅት ወይንም አክሲዮን ኩባንያ ነው፡፡

4.‹‹ **ደንብ** ››ማለት፡- በክልሉ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች እና ጥምረቶች ስለሚደራጁበትና ስለሚሰሩበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 84/2003 ነው፡፡

5.‹‹ **የሥነ ምግባር አውታር**››ማለት፡- በተሻሻለው የኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 142 የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ በመንግሥት መ/ቤቶች፣ በመንግሥት ልማት ድርጅቶች፣ በሕዝባዊ ተቋማት እና በሕብረተሰቡ ውስጥ ምግባረ ብልሹ ባህርያትን ለመቀነስ፣ መልካም ሥነ ምግባርን ለማስረጽና የፀረ ሙስና ትግሉን ለማስፋፋት የሚሠሩ አደረጃጀቶችን እና ክፍሎችን ያጠቃልላል፡

6.‹‹**የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረክ**››ማለት፡- በተቋማት እና በሕዝባዊ ማህበራት ተደራጅተው ለፀረ ሙስና ትግል ከኮሚሽኑ ጐን አጋር ሆነው የሚሰሩ አካላት ማለት ነው፡፡

7.‹‹**የፀረ ሙስና ጥምረት**››ማለት፡- ሙስናን በተባበረ ኃይል በጋራ ለመታገል ከመንግስት፣ ከመገናኛ ብዙሃን፣ከግሉ ዘርፍና ከሲቪል ማህበረሰብ የተወጣጡ አካላት በፈቃደኝነት በየደረጃው ከክልል እስከ ቀበሌ የመሠረቱት የፀረ ሙስና ግንባር ነው

8.‹‹**ፌዴሬሽን**››ማለት፡-በሴቶች የተቋቋሙ የተለያዩ አደረጃጀቶች በጋራ ስምምነት የፈጠሩት አንድነት ነው፡፡

9.‹‹ **ሊግ** ›› ማለት፡- በፖለቲካ አቋማቸው የተደራጁ የሴቶች አደረጃጀት ማለት ነው፡፡

10.‹‹ **ማህበር** ›› ማለት፡- የሴቶችን መብት ለማስከበርና ግዴታቸውን ለመወጣት እንዲችሉ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ለጋራ ዓላማ የተቋቋመ አደረጃጀት ነው፡፡

11.‹‹ **የሥነ ምግባር ኦፊሰር** ›› ማለት፡- የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ባለሙያ ሆኖ የሚያገለግል ሠራተኛ ነው፡፡

12.‹‹ **ሰው** ›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ለወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረክ አባል አደረጃጀቶችና በየሥራቸው የሚገኙ አባላትና ፈፃሚዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ የተቀመጡ ተግባራትን ለማሳካት በሚያደርጉት የጋራ እና የተናጠል እንቅስቃሴ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለመቋቋምና መደራጀት

## 5. ስለ ፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች መቋቋምና መደራጀት

1. የመስተዳድር ምክር ቤት ባወጣው *ደንብ ቁጥር 84/2003 ዓ.ም.* መሠረት የተለያዩ የሴቶች አደረጃጀቶች በጋራ ግንባር ፈጥረው እንዲንቀሳቀሱና የሥነ ምግባር አውታር ሆነው ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመታገል የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች በክልል፣ በዞን፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር፣ በቀበሌ ደረጃ ተቋቁመዋል፡፡
2. የልዩ ወረዳ/ወረዳ/ከተማ አስተዳደር ሴቶችና ህፃናት ጽ/ቤቶች የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮችን በቀበሌ ደረጃ ያቋቁማሉ፣
3. መድረኮቹ ሰብሣቢ፣ ምክትል ሰብሣቢ፣ ፀሐፊ እና አባላት ይኖሩታል፡፡

## 6. የመድረኩ አባላት

1. በእያንዳንዱ መድረክ የሚገኙ የሴቶች አደረጃጀቶች የመድረኩ አባል ይሆናሉ፣
2. የመድረኩ አባል አደረጃጀቶች የሥራ ኃላፊዎች/ተወካዮች የመድረኩ አመራር ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ፣
3. የመድረኩ አባል አደረጃጀት ዝርዝር

**ሀ. በክልል ደረጃ**

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የክልሉ ሴቶች እና ህፃናት ቢሮ ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የክልሉ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የክልሉ ሴቶች እና ህፃናት ቢሮ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | ፀሐፊ |
| 4 | የክልሉ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የክልሉ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | የክልሉ ም/ቤት ተመራጭ ሴት አባላት ፎረም /ኮኮስ/ አንድ ተወካይ | አባል |
| 7 | የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | አባል |
| 8 | ከኮሚሽኑየሥ /ም/ትም/አው/ማስተ/ዋና የሥራ ሂደት የአውታሮች ማስተባበሪያ ኬዝ ቲም አስተባባሪ | አባል |

### ለ. በዞን/በሀዋሣ ከተማ ደረጃ

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ ሴቶች እና ህፃናት መምሪያ ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ ሴቶች እና ህፃናት መምሪያ ፎካል ፐርሰን | ፀሐፊ |
| 4 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | የዞኑ/የሀዋሳ ከተማ ም/ቤት ሴት ተመራጭ አባላት ፎረም /ኮኮስ/ተወካይ | አባል |
| 7 | የዞኑ/የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር/ካንቲባ ጽ/ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | አባል |

### ሐ. በልዩ ወረዳ ደረጃ

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የልዩ ወረዳ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የልዩ ወረዳ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የልዩ ወረዳ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ፎካል ፐርሰን | ፀሐፊ |
| 4 | የልዩ ወረዳ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የልዩ ወረዳ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | የልዩ ወረዳ ም/ቤት ሴት ተመራጭ አባላት ፎረም /ኮኮስ/ተወካይ | አባል |
| 7 | የልዩ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | አባል |

**መ. በወረዳ ደረጃ**

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የወረዳ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የወረዳ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ሰብሣቢ |
| 3 | የወረዳ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ፎካል ፐርሰን | ፀሐፊ |
| 4 | የወረዳ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የወረዳ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | የወረዳ ም/ቤት ሴት ተመራጭ አባላት ፎረም /ኮከስ/ተወካይ | አባል |
| 7 | የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | አባል |

**ሠ. በሪፎርም ከተማ አስተዳደር ደረጃ**

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የከተማ አስተዳደር ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የከተማ አስተዳደር ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የሪፎርም ከተማ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ፎካል ፐርሰን | ፀሐፊ |
| 4 | የከተማ አስተዳደር ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የከተማ አሰተዳደር ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | የከተማ ም/ቤት ሴት ተመራጭ አባላት ፎረም /ኮከስ/ አንድ ተወካይ | አባል |
| 7 | የካንቲባ ጽ/ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰር | አባል |

ረ. በሀዋሣ ከተማ ክ/ከተሞች ደረጃ

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የክ/ከተማ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የክ/ከተማ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የክ/ከተማ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ፎካል ፐርሰን | ፀሐፊ |
| 4 | የክ/ከተማ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የክ/ከተማ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |

ሰ. በቀበሌ ደረጃ

| ተ.ቁ | የአባል አደረጃጀት ስም ዝርዝር | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | የቀበሌ ሴቶች ዘርፍ ኃላፊ | ሰብሣቢ |
| 2 | የቀበሌ ሴቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት | ም/ሰብሣቢ |
| 3 | የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ | ፀሐፊ |
| 4 | የቀበሌ ሴቶች ማህበር ሰብሳቢ | አባል |
| 5 | የቀበሌ ሴቶች ሊግ ሰብሳቢ | አባል |
| 6 | በቀበሌው የሚገኘው ት/ቤት ርዕሰ መምህር/በቀበሌው 2 ት/ቤት የሚገኝ ከሆነ የቀበሌው ካቢኔ አባል የሆነው ር/መምህር | አባል |

## 7. ስለተጨማሪ አባላት

በሁሉም አደረጃጀቶች ባሉ መድረኮች በአንቀጽ 6/3/ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ ረ እና ሰ በግልጽ ያልተመለከቱ ወይም ወደፊት የሚቋቋሙ ሌሎች አደረጃጀቶችን መድረኩ ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር የመድረኩ አባል እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 8. ተጠሪነትና የሥራ ግንኙነት

1. የቀበሌ መድረኮች ተጠሪነታቸው ለወረዳ/ለክፍለ ከተማ መድረክ እና ለቀበሌ አስተዳዳሪ ይሆናል፣
2. የወረዳ/የከተማ አስተዳደር ደረጃ መድረክ ተጠሪነቱ ለዞን መድረክ እና ለወረዳ አስተዳደሪ/ካንቲባ ይሆናል፣

3. የዞን፣ የልዩ ወረዳ እና የሀዋሣ ከተማ ደረጃ መድረክ ተጠሪነቱ ለክልል መድረክ እና ለዋና አስተዳዳሪ/ካንቲባ ይሆናል፣
4. የሀዋሣ ክ/ከተሞች መድረክ ተጠሪነት ለሀዋሣ ከተማ አስተዳዳር መድረክ እና ለክፍለ ከተሞች አስተዳዳሪዎች ይሆናል፣
5. የክልል መድረክ ተጠሪነቱ ለክልሉ ፀረ ሙስና ጥምረት ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ሲሆን ከኮሚሽኑ ጋር ቀጥተኛ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣
6. ኮሚሽኑ በየደረጃው ከሚገኙ መድረኮች ጋር እንደ አስፈላጊነቱ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣

## 9. የመድረኮች ተግባርና ኃላፊነት

### 1. በክልል ደረጃ ያሉ የመድረክ አባላት ተግባርና ኃላፍነት

1.1.ሙስና፣ የሥነ ምግባር ጉድለትና ብልሹ አሠራር በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ በማስጨበጥ በተለይ ሴቶች በፀረ ሙስና ትግል ግንባር ቀደም ተሣታፊ እንዲሆኑ ማስተባበር፣

1.2.ሴቶች ራሳቸውን በመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች እንዲያንፁ እና ከሙስና ራሳቸውን በማራቅ በኀብረተሰቡ ውስጥ መልካም አርአያ ሆነው እንዲታዩ ጥረት ማድረግ፣

1.3.ከኮሚሽኑ እንዲሁም ባሉበት ከተማ ከሚገኙ ከመንግሥት ተቋማት እና ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠርና በቅንጅት ሙስናን መከላከል፣

1.4.በሴቶች ዙሪያ የሚንቀሣቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ሙስና በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡና በዚህ ዙሪያ የሚደረገውን የፀረ ሙስና ትግል እንዲደግፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማስተባበር፣

1.5.በየደረጃው ካሉ መድረኮች ጋር በመተባበር በየዓመቱ በሚከበሩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፀረ ሙስና በዓላት የተለያዩ የኀብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበርና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነትና የሙስና አስከፊነት ማስተማር፣

1.6.የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የማስፋፋት ሥራ በሴቶች እና ህፃናት ሴክተር፣ በሴቶች ፌዴሬሽኖች፣ ሊጐችና ማህበራት ዕቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲተገበሩ ማስተባበር፣

1.7.በየአካባቢያቸው ከሙስና ጋር ተያያዥ የሆኑ ልማዳዊ አባባሎችን ነቅሶ በማውጣት መልካም ሥነ ምግባራዊ እሴቶች እንዲጐለብቱ እና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡

1.8.በታችኛው እርከን የሚገኙ መድረኮችን የመከታተል፣ የመደገፍና ግብረ መልስ መስጠት፣

1.9.የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የመድረኮችን ተግባርና ኃላፊነታቸውን በበቂ ሁኔታ መወጣት እንዲችሉ የሥልጠና ፍላጐት በመለየት ሥልጠናዎች ማመቻቸት፣

1.10.መድረኩ ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያግዝ የውስጠ ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር፣

1.11.ከመድረኮቹ የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለሌሎች ማስፋት፣

1.12.በየአደረጃጀቶቻቸው የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችንና ብልሹ አሠራሮችን በመከታተል ሙስና ተፈጽሞ ሲገኝ ትክክለኛና ተአማኒነት ያለው ጥቆማ ለኮሚሽኑ መስጠት፣

1.13.መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ልምድ በማሳደግ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍ፣

1.14.የመድረኩን እቅድና የክንውን ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለኮሚሽኑና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣

1.15.ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር በቅንጅት መስራት፣

1.6.በየወቅቱ የመድረኮችን አፈጻጸም የመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃቸውን መለየት፣

1.7.መድረኩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ከኮሚሽኑ የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን፣

## 2. የዞን/የሀዋሣ ከተማ ደረጃ ያሉ የመድረክ አባላት

2.1.ሙስና፣ የሥነ ምግባር ጉድለትና ብልሹ አሠራር በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ በማስጨበጥ በተለይ ሴቶች በፀረ ሙስና ትግል ግንባር ቀደም ተሣታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና መቀስቀስ፣

2.2.ሴቶች ራሳቸውን በመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች እንዲያንፁ እና ከሙስና ራሳቸውን በማራቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ መልካም አርአያ ሆነው እንዲታዩ ጥረት ማድረግ፣

2.3.ከክልሉ መዋቅር እንዲሁም ባሉበት ከተማ ከሚገኙ የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሴክተር እና ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠርና በቅንጅት ሙስናን መከላከል፣

2.4.በሴቶች ዙሪያ የሚንቀሣቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ሙስና በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡና በዚህ ዙሪያ የሚደረገውን የፀረ ሙስና ትግል እንዲደግፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማስተባበር፣

2.5.ከወረዳ/ከከተማ አስተዳደር መድረኮች ጋር በመተባበር በየአመቱ በሚከበሩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፀረ ሙስና በዓላት እንዲከበሩ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማስተባበር የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነትና የሙስና አስከፊነት ማስተማር፣

2.6.የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የማስፋፋት ሥራ በሴቶች እና ህፃናት ሴክተር፣ በሴቶች ፌዴሬሽኖች፣ ሊጎችና ማህበራት ዕቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲተገበሩ ማስተባበር፣

2.7.በየአካባቢያቸው ከሙስና ጋር ተያያዥ የሆኑ ልማዳዊ አባባሎችን ነቅሶ በማውጣት መልካም ሥነ ምግባራዊ እሴቶች እንዲጐለብቱ እና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡

2.8.በታችኛው እርከን የሚገኙ መድረኮችን የመከታተል፣ የመደገፍና ግብረ መልስ መስጠት፣

2.9.የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማስተባበር ለመድረኮቹ ሥልጠና ማመቻቸት፣

2.10.መድረኩ ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያግዝ የውስጠ ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር፣

2.11.ከመድረኮቹ የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለሌሎች ማስፋት፣

2.12.በየአደረጃጀቶቻቸው የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችንና ብልሹ አሠራሮችን በመከታተል ሙስና ተፈጽሞ ሲገኝ ትክክለኛና ተአማኒነት ያለው ጥቆማ ለኮሚሽኑ መስጠት፣

2.13.መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ልምድ በማሳደግ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍ፣

2.14.የመድረኮቹን እቅድና የክንውን ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለክልሉና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣

2.15.ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር በቅንጅት መሥራት፣

2.16.በየወቅቱ የመድረኮችን አፈጻጸም መገምገምና የአፈጻጸም ደረጃቸውን መለየት፣

2.17.መድረኩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ከኮሚሽኑ እና ከክልሉ መድረክ የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን፣

## 3. በልዩ ወረዳ/በወረዳ/በሪፎርም ከተሞች ደረጃ ያሉ የመድረክ አባላት

3.1.ሙስና፣ የሥነ ምግባር ጉድለትና ብልሹ አሠራር በሴቶች ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚያደርሰውን ጉዳት በስፋት ማስተማር በተለይ ሴቶች በፀረ ሙስና ትግል ግንባር ቀደም ተሣታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

3.2.ሴቶች ራሳቸውን በመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች እንዲያንፁ እና ከሙስና ራሳቸውን በማራቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ መልካም አርአያ ሆነው እንዲታዩ ጥረት ማድረግ፣

3.3.በልዩ ወረዳ/ወረዳ/በሪፎርም ከተሞች ከሚገኙ አስተዳደር አካላት እና ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠርና በቅንጅት ሙስናን መከላከል፣

3.4.በሴቶች ዙሪያ የሚንቀሣቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ሙስና በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡና በዚህ ዙሪያ የሚደረገውን የፀረ ሙስና ትግል እንዲደግፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማስተባበር፣

3.5.በተደራጁበት አካባቢ መድረኮች ጋር በመተባበር በየአመቱ ለሚከበሩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፀረ ሙስና በዓላት እንዲከበሩ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነትና የሙስና አስከፊነት ማስተማር፣

3.6.የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የማስፋፋት ሥራ በሴቶች እና ህፃናት ሴክተር፣ በሴቶች ፌዴሬሽኖች፣ ሊጐችና ማህበራት ዕቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲተገበሩ ማስተባበር፣

2.7.በታችኛው እርከን የሚገኙ መድረኮችን የመከታተል፣ የመደገፍና ግብረ መልስ መስጠት፣

2.8.የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማስተባበር ለመድረኮቹ ሥልጠና ማመቻቸት፣

3.9.በየአካባቢያቸው ከሙስና ጋር ተያያዥ የሆኑ ልማዳዊ አባባሎችን ነቅሶ በማውጣት መልካም ሥነ ምግባራዊ እሴቶች እንዲጐለብቱ እና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፡

3.10.መድረኩ ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያግዝ የውስጠ ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር፣

3.11.ከመድረኮቹ የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችንና ተሞክሮችን ቀምሮ ለሌሎች ማስፋት፣

3.12.በየአደረጃጀቶቻቸው የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችንና ብልሹ አሠራሮችን በመከታተል ሙስና ተፈጽሞ ሲገኝ ትክክለኛና ተአማኒነት ያለው ጥቆማ ለኮሚሽኑ መስጠት፣

3.13.መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ልምድ በማሳደግ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍ፣

3.14.የመድረኩን እቅድና የክንውን ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለዞኑ/ለሀዋሣ ከተማና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣

3.15.ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር በቅንጅት መስራት፣

3.16.በየወቅቱ የመድረኮችን አፈጻጸም የመገምገምና የአፈጻጸም ደረጃውን የመለየት ሥራ መስራት፣

3.17.መድረኩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ከኮሚሽኑ፣ ከክልል፣ ከዞንና ከሀዋሣ ከተማ መድረኮች የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን፣

## 4. በቀበሌ/በሀዋሳ ከተማ ክፍለ ከተማ ደረጃ ያሉ የመድረክ አባላት

4.1.ሙስና፣ የሥነ ምግባር ጉድለትና ብልሹ አሠራር በሴቶች ላይ እንዲሁም በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚያደርሰውን ጉዳት በስፋት ማስተማር በተለይ ሴቶች በፀረ ሙስና ትግል ግንባር ቀደም ተሣታፊ እንዲሆኑ ማበረታታትና ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

4.2.ሴቶች ራሳቸውን በመልካም ሥነ ምግባር እሴቶች እንዲያንፁ እና ከሙስና ራሳቸውን በማራቅ በኅብረተሰቡ ውስጥ መልካም አርአያ ሆነው እንዲታዩ ጥረት ማድረግ፣

4.3.ከወረዳ እንዲሁም ባሉበት ቀበሌ ከሚገኙ አስተዳደር አካላት እና ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት መፍጠርና በቅንጅት ሙስናን መከላከል፣

4.4.በቀበሌ/ክፍለ ከተማ በሴቶች ዙሪያ የሚንቀሣቀሱ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ሙስና በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡና በዚህ ዙሪያ የሚደረገውን የፀረ ሙስና ትግል እንዲደግፉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና ማስተባበር፣

4.5.በተደራጁበት አካባቢ መድረኮች ጋር በመተባበር በየአመቱ በሚከበሩ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የፀረ ሙስና በዓላት ላይ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ስለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊነትና የሙስና አስከፊነት ማስተማር፣

4.6.የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት የማስፋፋት ሥራ በቀበሌው ሴቶች ፌዴሬሽን፣ ሊግና ማህበር ዕቅድ ውስጥ ተካቶ እንዲተገበሩ ማስተባበር፣

4.7.በቀበሌው ከሙስና ጋር ተያያዥ የሆኑ ልማዳዊ አባባሎችን ነቅሶ በማውጣት የመልካም ሥነ ምግባራዊ እሴቶች እንዲጐለብቱ እና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣

4.8.መድረኩ ከራሱ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ተግባርና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያግዝ የውስጠ ደንብ ማዘጋጀትና መተግበር፣

4.9.በቀበሌው/ክፍለ ከተማና በአከባቢው የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎችንና ብልሹ አሠራሮችን በመከታተል ሙስና ተፈጽሞ ሲገኝ ትክክለኛና ተአማኒነት ያለው ጥቆማ ለኮሚሽኑ መስጠት፣

4.10.መረጃ አደራጅቶ የመያዝ ልምድ በማሳደግ ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ ትክክለኛ መረጃ ማስተላለፍ፣

4.11.የመድረኩን እቅድና የክንውን ሪፖርቶች በማዘጋጀት ለወረዳ/ለህዋሳ ከተማ እና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፣

4.12.ከሌሎች የሥነ ምግባር አውታሮች ጋር በቅንጅት መሥራት፣

4.13.መድረኩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት የሚረዱ ከኮሚሽኑ፣ ከዞን፣ ከወረዳ መድረኮች የሚሰጡ ሌሎች ተጨማሪ ተግባራትን ማከናወን፣

## 10. የመድረኩ ሰብሣቢ፣ ምክትል ሰብሣቢ፣ ፀሐፊና አባላት ተግባርና ኃላፊነት

### 1. የመድረኩ ሰብሣቢ ተግባርና ኃላፊነት

1.1.የመድረኩን አጠቃላይ እንቅስቃሴ በመወከል ይመራል፣

1.2.ከፀሐፊው ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣

1.3.የመድረኩን አባላት ስብሰባ ይጠራል፣

1.4.የመድረኩን ረቂቅ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለአመራር አባላት በማቅረብ ያስወስናል፣ ይህንኑ ተጠሪ ለሆነበት መድረክ ያሣውቃል፣

1.5.ስለመድረኩ እንቅስቃሴ ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ያደርጋል፣

1.6.ስለመድረኩ የሥራ እንቅስቃሴ ከኮሚሽኑና በተዋረድ ተጠሪ ከሆነበት መድረክ ጋር ይመካከራል፣

1.7.የመድረኩ አባላት ማናቸውም የመድረኩ የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ጥረት ያደርጋል፣

1.8.ለመድረኩ ሥራ መሳካት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር ለመድረኩ ሥራ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጥራል፣

1.9.አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መድረኩ ለሚያዘጋጀው ስልጠናዎች፣ ሴሚናሮች አውደ ጥናቶችና ለመሰል ጉዳዮች የሚረዱ የፋይናንስም ሆነ ሌሎች ግብዓቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የተገኘውን የፋይናንስ ድጋፍ አግባብ ባለው የፋይናንስ ህግ መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

1.10.የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ትምህርት የማስፋፋት ሥራ በአባል አደረጃጀቶች ዕቅድ ውስጥ መካተቱን እና መተግበሩን ይከታተላል፣

1.11.ከኮሚሽኑና ተጠሪ ከሆነበት መድረክ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

## 2. የመድረኩ ምክትል ሰብሣቢ ተግባርና ኃላፊነት

2.1.ሰብሣቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

2.2.የመድረኩ ፀሐፊ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

2.3.ሌሎች ከሰብሣቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

## 3. የመድረኩ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

3.1.የመድረኩን ጽ/ቤት በተገቢው ያደራጃል ቋሚ ጽ/ቤት በሌለበት ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር የመድረኮቹ ሠነዶች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ያመቻቻል፣

3.2.ለመድረኩ አባላት የስብሰባ ጥሪ ደብዳቤ በማዘጋጀት ያሰራጫል፣

3.3.ለመድረኩ ስብሰባ የሚሆኑ አጀንዳዎችን ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፣

3..4.በስብሰባ ሰዓት ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣

3.5.የመድረኩን ማንኛውንም ሠነዶች በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

3.6.በሪፖርት ዝግጅት ወቅት ከሰብሣቢው ጋር በመመካከር ይሰራል፣ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ጥረት ያደርጋል፣

3.7.ሌሎች በሰብሣቢው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፣

## 4. የመድረኩ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

4.1.በማናቸውም የመድረኩ የተግባር እንቅስቃሴ በንቃት ይሳተፋሉ፣

4.2.መደበኛም ሆነ አስቸኳይ ስብሰባ ሲጠሩ ይገኛሉ፣

4.3.በስብሰባ ወቅት ጠቃሚ ሀሣቦችን ያመነጫሉ፣

4.4.ለመድረኩ መጠናከር ጠቃሚ ናቸው የሚሏቸውን ሀሣቦች አጀንዳ በማስያዝ ለውይይት ያቀርባሉ፣

4.5.ለእያንዳንዱ የመድረኩ አባል ተቋም የሴክተሩን የሥራ እንቅስቃሴ በመደገፍ፣ በመከታተልና በመገምገም ሳለበት መድረክ ሪፖርት ይዞ ይቀርባል፣

4.6.የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ በየተቋሞቻቸው እየተደረጉ ያሉ እንቅስቃሴዎችን ለመድረኩ እና ለሚመለከታቸው አካላት በጽሑፍ ሪፖርት ያደርጋሉ፣

## 11. የመድረኩ አመራር አባላት መብትና ግዴታ

### 1. መብት

ሀ.በመድረኮቹ ስብሰባዎች ሀሣባቸውን በነጻነት የማቅረብና የማንሸራሸር፣

ለ.ተግባርና ኃላፊነታቸውን በሚመለከት ግልጽነት በጐደላቸው ጉዳዩች በተዋረድ ተጠሪ ከሆኑበት አካል እና ኮሚሽኑን በመጠየቅ ምላሽ የማግኘት፣

ሐ.መድረኮቹ በተደራጁበት አካባቢ በነጻነት ተንቀሳቅሰው የማስተማርና ግንዛቤ የመፍጠር፣

መ.በመድረኮቹ የውስጥ አሠራር መሠረት አጀንዳ ማስያዝ፣

ሠ.በኮሚሽኑና ተጠሪ ከሆኑበት መድረክ ሥልጠና የማግኘት መብት፣

ረ.የተጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት ያልቻሉ አመራር አባላት በወከሉት አደረጃጀት ውስጠ ደንብ እና መመሪያ በሚያዘው መሠረት ውሣኔ እንዲሰጥበት ለወከሉት አካል የመድረኩን የጋራ ውሣኔ ሀሣብ በጽሁፍ የማቅረብ፣ ይህንኑ በግልባጭ ኮሚሽኑ እንዲያውቅ ይደረጋል፡፡

### 2. ግዴታ

ሀ.በዚህ መመሪያ መሠረት የሚተላለፉ ውሣኔዎችን ተፈጻሚ የማድረግ፣

ለ.ለመድረኩ ዓላማ መሳካት አቅማቸውን አሟጠው በመጠቀም የተጣለባቸውን ኃላፊነት የመወጣት፡፡

ሐ.የስብሰባ ጥሪን አክብሮ መገኘት፣

መ.የሙስና ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ለኮሚሽኑ የመጠቆም፣

ሠ.ስለ ሥራቸው ለመድረኩ ሰብሳቢ ሪፖርት የማድረግ፣

ረ.ተአማኒነት ያለውን መረጃ የመስጠት፣

## 12..የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. ተቋማዊ በሆነ መልኩ የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች አደረጃጀቶችንና አሠራር ማጠናከር፣
2. የመድረኮቹን አቅም ለማጐልበት የሥልጠና መስጠት፣
3. የሚመለከታቸውን አካላት በማስተባበር የመድረኩን ውጤታማነትና ዘላቂነት ለማረጋገጥ መሥራት፣
4. መድረኮቹ የሚገኙበት ዞን፣ ልዩ ወረዳ፣ ከተማ አስተዳደር፣ ወረዳ አስተዳደር፣ቀበሌ/ክፍለ ከተማ አስተዳደርና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ለመድረኮቹ ምቹ ሁኔታ እንዲፈጥሩ እና መድረኮቹ ከአካባቢው መንግሥታዊ መዋቅር ጋር ጠንካራ ትስስር እንዲኖራቸው ማድረግ፣

5. ከመድረኮቹ የሚገኙ ጠቃሚ ልምዶችንና ተሞክሮዎችን ቀምሮ ለሌሎች የማስፋት፣
6. ለመድረኮቹ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ፣
7. የተሻለ አፈጻጸም ላላቸው የንቅናቄ መድረኮች የሚበረታቱበትን ሁኔታ የማመቻቸት፣
8. የመድረኮቹ ልምድ መለዋወጫ አመታዊ ኮንፈረንስ እንዲካሄድ ማመቻቸት፣

### 13. የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

1. መድረኩ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በስብሰባ ላይ ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው ($^2/_3$ኛው) ከተገኘ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
3. የመድረኩ ውሣኔ የሚተላለፈው በስብሰባ ከተገኙ አባላት በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም የሁለቱ ወገን ድምጽ እኩል ከሆነ ሰብሣቢው ያለበት ወገን አቋም የመድረኩ ውሣኔ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 14.የጋራ ጉባኤዎች

1.በተዋረድ የሚገኙ የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች የፀረ ሙስና ትግል ሂደት በየሩብ ዓመቱ በመገምገም ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን በመለየት ቀጣይ አቅጣጫ ያስቀምጣሉ፣

2.ከኮሚሽኑ ጋር በዓመት አንድ ጊዜ በሚደረገው ስብሰባ ላይ ከመድረኩ የሚመለከታቸው አካላት ይሳተፋሉ፣

3.በዓመታዊ ጉባኤ የተጠቃለለ ሪፖርት የክልሉ መድረክ ያቀርባል፣

## 15.የጋራ ጉባኤ አመራር አካላትና የጉባኤው አዘገጃጀት

## 15.1.የጋራ ጉባኤው አመራር አካላት

ሀ.በክልል ደረጃ በኮሚሽኑ አዘጋጅነት በሚካሄደው ጉባኤ የክልል፣ የዞኖች/የሀዋሳ ከተማ እና የልዩ ወረዳዎች የመድረኩ ሰብሳቢዎች በዋናነት የሚሳተፉ ሲሆን ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች አመራሮችም እንድሳተፉ ልያደርግ ይችላል፣

ለ.ኮሚሽኑ እንደአስፈላጊነቱ ባለድርሻ የሆኑ አከላትንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትን በጉባኤው እንዲሳተፉ ጥሪ ሊያስተላልፍ ይችላል፣

ሐ.ዞኖች፣ ሀዋሳ ከተማ እና ልዩ ወረዳዎች በሚያዘጋጁት ጉባኤ በተዋረድ የሚገኙ መድረኮች አመራር አካላትን ሊያሳትፉ ይችላሉ፣

## 15.2.የጉባኤው አዘገጃጀት

ሀ.በኮሚሽኑ አዘጋጅነት በዓመት አንድ ጊዜ የጋራ ጉባኤ ይካሄዳል፣

ለ.በክልል መድረክ አዘጋጅነት በየ6 ወሩ ይካሄዳል፣

ሐ.በዞን፣ በሀዋሳ ከተማ፣ በልዩ ወረዳ፣ በወረዳና ሪፎርም ከተሞች የሚገኙ መድረኮችም ከላይ በ‹‹ለ››የተገለፀውን አሠራር በመከተል ያካሂዳሉ፣

## 16.ከሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰሮች የሚጠበቅ ድጋፍ

በየደረጃው ባሉ ተቋማት የሚገኙ የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ኦፊሰሮች በትብብርና ቅንጅት ፎረማቸው አማካይነት የመድረኮቹን አፈፃፀም ከመገምገም ባለፈ ሁለንተናዊ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፣

## 17.ስለመተባበር

መድረኮቹ በሚቋቋሙበት አካባቢ የሚገኙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ልማት ድርጅቶች ወይም ሕዝባዊ ተቋማት የንቅናቄ መድረኮች ለሚያከናውኑት ተግባር ሁኔታው የሚጠይቀውንና አቅማቸው የሚፈቅደውን የመተባበር ግዴታ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 18.ለፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች ስለሚሰጥ የህግ ከለላ

የተለያዩ የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች በሚያካሄዱት የፀረ ሙስና ትግል ምክንያት ጥቃት፣ ዛቻ፣ ትንኮሳ እና መሰል ድርጊቶች የሚፈፀምባቸው ሰዎች *በደንብ ቁጥር 84/2003 አንቀጽ 12-14* የተደነገጉት የጥበቃ እርምጃዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

## 19.የኮሚሽኑና የመድረኮቹ የግንኙነት አግባብ

1. መድረኮቹ ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው ለሚመለከተው በተዋረድ ተጠሪ ለሆኑበት መድረክ ያቀርባሉ፤
2. በዕቅዳቸው መሠረት የክንውን ሪፖርት የየሩብ ዓመት፣ የ6 ወር፣ የዓመቱን ሪፖርት እያንዳንዱ መድረክ በተዋረድ ተጠሪ ለሆኑበት መድረክ ያቀርባል፣
3. የክልሉ መድረክ የተጠቃለለ ሪፖርት ለኮሚሽኑ ያቀርባል፣
4. ኮሚሽኑ በክልል፣ በዞን፣ በሀዋሳ ከተማ እንዲሁም በናሙናነት በተመረጡ የወረዳ/የከተማ መድረኮች ክትትልና ድጋፍ የሚያደርግ ሆኖ ከክልል ጀምሮ እስከታችኛው እርከን ከሚገኙ መድረኮች ጋር እንደአስፈላጊነቱ በአካልና በስልክ የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣
5. ኮሚሽኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና በሚያዘጋጅበት ወቅት እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለማስተላለፍ በሚፈለግበት ጊዜ ከክልሉ መድረክ ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡
6. የሴቶች የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች የልምድ ልውውጥ የጋራ መድረክ በዓመት አንድ ጊዜ በሚዘጋጅበት ወቅት መድረኮች እርስ በእርስና ከኮሚሽኑ ጋር የሚገናኙበት የጋራ መድረክ ይፈጠራል፡፡

## 20.ሌሎች ሁኔታዎች

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍሎች፣ የፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች እና ጥምረቶች ስለሚደራጁበትና ስለሚሰሩበት ሁኔታ ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ ደንብ ቁጥር 84/2003 ስለንቅናቄ መድረኩ አባላት የተመለከቱ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚ ናቸው፡፡

## 21.ቅጣት

ይህን መመሪያ በማያከብሩ እና የተጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት ባልቻሉ አመራር አባላት የወከሉት አደረጃጀት ውስጠ ደንብ እና መመሪያ በሚያዘው መሠረት እንዲሁም በሌሎች አሰራሮች ተጠያቂ ይሆናል፤ ይህንኑ በግልባጭ ኮሚሽኑ እንዲያውቀው ይደረጋል፡

## 22.ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎችና አሠራሮች

ስለ ፀረ ሙስና ንቅናቄ መድረኮች አደረጃጀትና አሠራር ለመወሰን የወጣው መመሪያ ቁጥር 13/2003 እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሌሎች አሠራሮች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

## 23.መመሪያን ስለማሻሻል

ይህንን መመሪያ ኮሚሽኑ ከመድረኮቹ አፈፃፀምና መግባባት በመነሳት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 24.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 05 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አባይነህ አዴቶ**

***የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት***

***የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር***